# ልጄ በነጻ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ክትባት ማግኘት ይችላልን/ትችላለችን?

## የታካሚ የራስ-በራስ መመርመሪያ ቅጽ

የሚኒሶታ የሕጻናት ክትባት (Minnesota Vaccines for Children, MnVFC) ፕሮግራም ዕድሜአቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በታች ላሉ ልጆች በነጻ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ክትባት ይሰጣል።

ልጅዎን የሚመለከተውን ቀጥሎ በተዘረዘሩት ፈርጆች አጠገብ ካለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። የተሞላውን ቅጽ ለዶክተርዎ ወይም ክሊኒክዎ ይስጡ።

እባክዎን ልብ ይበሉ፦ የሐኪም ቀጠሮ ክፍያዎች፣ ክትባት የመከተቢያ ክፍያ እና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች በዚህ ፕሮግራም አይሸፈኑም።

1. ☐ **ልጄ የጤና ኢንሹራንስ የለውም/የላትም**

   ልጅዎ ለየሚኒሶታ የሕጻናት ክትባት (MnVFC) ብቁ ነው/ናት።

2. ☐ **ልጄ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በመሳሰሉ የሚኒሶታ የጤና እንክብካቤ ፕሮግራም (Minnesota Health Care Program) አለ/ች፦**

   Medical Assistance (የሕክምና እርዳታ)

   MinnesotaCare (ሚኔሶታኬር)

   Prepaid Medical Assistance Plan (ቀድሞ የተከፈለ የሕክምና እርዳታ ፕላን)

   ልጅዎ ለየሚኔሶታ የሕጻናት ክትባት (MnVFC) ብቁ ነው/ናት።

3. ☐ **ልጄ አሜሪካን ኢንዲያን/የአላስካ ተወላጅ ነው/ናት።**

   ልጅዎ ለየሚኔሶታ የሕጻናት ክትባት (MnVFC) ብቁ ነው/ናት።

4. ☐ **ልጄ የሁሉንም ክትባቶች ወጪ የሚሸፍን የግል የጤና ኢንሹራንስ አለው/አላት፤ ነገር ግን የክትባቶቹ ወጪ ከመሸፈኑ በፊት በባለኢንሹራንሱ የሚከፈለውን ተቀናሽ ክፍያ መክፈል ይኖርብኝ ይሆናል።** (እርግጠኛ ካልሆኑ ወደ 5ኛ ፈርጅ ይሂዱ)።

   ኢንሹራንስዎ የክትባቶቹን ወጪ ሸፍኗል። ልጅዎ ለየሚኔሶታ የሕጻናት ክትባት (MnVFC) ብቁ አይደለም/ችም።

5. ☐ **ልጄ የግል የጤና ኢንሹራንስ አለው/አላት፤ ነገር ግን የክትባት ወጪ ይሸፍን እንደሆነ አላውቅም።**

   በኢንሹራንስ ካርድዎ ጀርባ ላይ የሚገኘውን የስልክ ቁጥር በመጠቀም ለኢንሹራንስ ኩባኒያዎ ይደውሉ። ያልዎት ፕላን ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ማናቸውም ዘርፎች ጋር ይስማማ እንደሆነ ይጠይቁ።

   አንድ ወይም ከዚያ በላይ ክትባቶች አይሸፍንም።

   በሕዝብ ክሊኒክ* ለ MnVFC ብቁ ለሆኑ ሽፋን-ለሌላቸው ክትባቶች ብቻ።

   የተወሰነ ዋጋ ለ ሲ.ኤ.ፒ.ኤስ (Caps) መከላከያ አገልግሎቶች።

   ያ ዋጋ በደረሰ ጊዜ፤ ልጅዎ በሕዝብ ክሊኒክ* ለ *MnVFC* ብቁ ይሆናል/ትሆናለች።

   የሁሉንም ክትባቶች ወጪ ይሸፍናል፤ ነገር ግን የክትባቶቹ ወጪ ከመሸፈኑ በፊት በባለኢንሹራንሱ የሚከፈለው ተቀናሽ ክፍያ መክፈል አለበት።

   ኢንሹራንስዎ የክትባቶቹን ወጪ ሸፍኗል። ልጅዎ ለየሚኔሶታ የሕጻናት ክትባት *(MnVFC)* ብቁ አይደለም/ችም።

* ልጅዎ ከሚከተሉት ከእነኚህ የሕዝብ ክሊኒኮች በአንዱ በነጻ ወይም በአነስተኛ ዋጋ ክትባት ለማግኘት ብቁ ነው/ናት : በአካባቢ የሕዝብ ጤና ክሊኒኮች (local public health clinics) (LPH)፣ በፌዴራል ደረጃ ብቁ የሆኑ የጤና ማዕከላት (Federally Qualified Health Centers, FQHC)፣ የገጠር ጤና ማዕከላት (Rural Health Centers, RHC)፣ ኢንዲያን የጤና አገልግሎት (Indian Health Service, IHS)፣ እና የጎሳ የጤና ክሊኒኮች (tribal health clinics).

Minnesota Department of Health
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164
651-201-5522
health.mnvfc@state.mn.us
www.health.state.mn.us/vfc

4/19/23 (Amharic)

*ይህንን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት ይደውሉ: 651-201-5522 or 1-800-657-3970.*